ላስ ቬጋስ ስማ ሰምተህም አሰማ!!!

ቤት ለቤት እየመጡልህ ነው !!!

በገዳ ሥርዓት ኢትዮጵያንናን የኢትዮጵያን ሕዝብ በማጥፋት አዲስ አበባንም በመዋጥ ላይ የሚገኘውን ዘረኛ የኦሮሙማ መንግሥት ለማጠናከር በኮረና ቫይረስ ተጠቂዎች ስም ከዲያስፖራው ላይ ገንዘብ ማሰባሰባቸውን ቀጥለዋል። በአምባሳደር ፍፁም አረጋ የሚመራው ይህ አንጃ በተለያዩ እስቴቶች ባንዳዎችን በመመልመል ከወያኔ ለባሰው ለኦሮሙማ ዘረኛው መንግሥት ማጠናከሪያ የሚሆን ገንዘብ በኮረና ቫይረስ ተጠቂዎች ስም የዲያስፖራውን ኪስ እያራቆተ ነው። ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ከኮረና ቫይረስ ተጠቂዎች ጀርባ ያለውን ደባ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ በሆኑ ወገኖች በኩል እንዲነቁ ተደርጓል። ይሁን እንጂ በአምባሳደር ፍፁም አረጋ የሚመራው ባንዳ ደባው እየተናቃበት መምጣቱን ስለ ተረዳ በሶሻል ሚዲያና በቴሌ ኮንፍረንስ ያሰማራቸው ባንዳዎች ማሊያና እስትራቴጂ እየቀያየሩ የየዋህ ኢትዮጵያውያንን ኪስ እያራቆቱ ነው። በየእስቴቱ የሚገኙት አንዳንድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲዎችን፣ የሲቪክ ማህበራትን፣ የኢዜማ ድርጅትንና ሌሎችን በጥቅማ ጥቅም እየገዙ የዲያስፖራውን ማህበረሰብ እያጭበረበሩ ነው።

በላስ ቬጋስ የኢትዮጵያ ኮሚውኒቲ የኢዜማና አንዳንድ የሲቪክ ማህበራትን በባንዳነት በመመልመል ዲያስፖራውን ማጭበርበራቸውን ቀጥለውበታል። ከላስ ቬጋስ እስቴት ሕግ ውጪ እና ከላስ ቬጋስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ መተዳደሪያ ሕግና ደንብ ውጪ የላስ ቬጋስ ኮሚዩኒቲ የዘረኛው የኦሮሙማ መንግሥት ፖሊሲ አስፈፃሚ መሆናቸው ውሎ ያደረ ደባ ከመሆኑም ባሻገር ከላስ ቬጋስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ የሕዝብ ገንዘብ ላይ ሕዝቡ ሳያውቅና ሳይፈቅድ በተለያዩ ወጪዎች ስም አድርገው በማውጣት ለዘረኛው የኦሮሙማ መንግሥት የሕዝቡን ገንዘብ ደብቀው እንደሰጡ የውስጥ አዋቂዎች አጋልጠዋል።

ይሄ ሁሉ አልበቃ ብሏቸው በአሁኑ ወቅትም የላስ ቬጋስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በየግለሰቡ ቤት ስልክ እየደወሉ በኮረና ቫይረስ ተጠቂዎች ስም ገንዘብ ካላመጣችሁ እያሉ የላስ ቬጋስን ሕዝብ እያስጨነቁ ነው። በስራ ማጣትና በኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ አጣብቂኝ ውስጥ የሚገኘውን የላስ ቬጋስን ሕዝብ ቤት ለቤት እየደወሉ ገንዘብ ካላዋጣችሁ እያሉ በማስጨነቅ ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ የላስ ቬጋስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ አባላትና ሌላው ማህበረሰብ እንደዚሁም በሌሎች እስቴቶች የምትገኙ ሀገር ወዳድ እትዮጵያውያኖች በሙሉ ይህንን የማንቂያ ደውል እንድታሰሙና እንድታስተላልፉ፤ ኮሚዩኒታችሁንና ማህበራች ሁን እንድትታደጉ እናሳስባለን እናመሰግናለን።